# (13) የገላትያ መልዕክት-2

## ጥናት አንድ ገላትያ 1፡1-10

የጥናት ዓላማ፡- ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱን አሳልፎ የሰጠለት ይህ ወንጌል ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ የምናስተላልፈው መልካም የምስራች እንጂ በዘፈቀደ መልዕክቱን እኛ በተመቸን መንገድ መቀያየር የምንችለው ነገር እንዳልሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ነገር ግን እኛም ብንሆን ወይም የሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ እርሱ ለዘላለም የተረገመ ይሁን… ማንም ከተቀበላችሁት ሌላ የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ፣ እርሱ ለዘላለም የተረገመ ይሁን።" ገላ 1፡8-9

1. ገላትያ 1፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2ትን ስናነብ የዚህ የገላትያ መልዕክት ጸሐፊ ማን እንደሆነ ነው የምንረዳው? "አብረውኝም ካሉት ወንድሞች ሁሉ" የሚለው አነጋገር ደብዳቤውን በመጻፍ አብረውት የነበሩት ወንድሞች ሁሉ ተሳታፊዎች ነበሩ ማለቱ ነው ወይስ ምን ለማለት ለማለት ፈልጎ ነው ብለህ ታምናለህ?
2. ከላይ ባየናቸው ሁለት ቁጥሮች ላይ ጳውሎስ የሐዋርያነቱ መሰረት ከምን እንደመነጨ ያስረዳል። ጳውሎስ ሐዋርያነቱን ከየት እንዳገኘው ለአንባቢዎቹ ማረጋገጥ ያስፈለገው ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? ይህ ሰው ሐዋርያነቱ ከየት እንደተገኘ ብቻ ሳይሆን፤ ከየት እንዳልተገኘም ጭምር ሲያስረዳ ምን በማለት ነው የሚናገረው?
3. ቁ3-5 ላይ ጳውሎስ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት አስመልክቶ ሲናገር፤ በዚህ ሥፍራ የእግዚአብሄር አብን ተሳትፎ እንዴት አድርጎ ነው ያቀረበልን? አብዛኛውን ጊዜ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ሲነገር የገደሉት ሰዎች እንደሆኑ ነው የምናውቀው፤ ታዲያ ቁ4ትን ስናነብ ከጳውሎስ አነጋገር ይህንን ሃሳብ በተመለከተ ምን የተለየ ነገር ይጠቁመናል?
4. ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ሰው ልጆች ራሱን ስለሰጠበት ምክንያት መጽሐፍ ቅዱሳችን ብዙ ዓይነት ነገሮችን ይነግረናል። ቁ4ትን ተመርኩዘን ስንመለከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለእኛ ስለሰጠበት ምክንያት ምን እናያለን? ቁ4 ላይ "ከዚህ ክፉ ዓለም ያድነን ዘንድ" ስለሚለው ሃሳብ የምትረዳው ምንድነው? ክፉውን ዓለም ለማሸነፍ እንድትችል የክርስቶስ ሞት ያንንም እንደሚጨምር መረዳትህ ምን ያህል ነው?
5. ቁ6 ላይ ስናይ የገላትያ ሰዎች ያደረጉት ነገር ጳውሎስን እንዳስደነቀው እናነባለን፤ እነዚህ ሰዎች ያደረጉት ነገር ለምንድነው ይኸንን ያህል እንደ ትልቅና ከባድ ነገር ሆኖ ሐዋርያው እስኪደነቅ ድረስ ያደረሰው ብለህ ታምናለህ? እነዚህ ሰዎች የተቀበሉትን ትምህርት የተለየ ወይም ልዩ ወንጌል ያሰኘው ነገር ምንድነው?
6. በቁ6 ላይ ሌላ ወንጌል በማለት እየጠራው፤ በቁ7 ላይ ደግሞ ሌላ ወንጌል የሚባል ነገር የለም ማለቱ ተቃራኒ ሃሳብ አይሆንም ወይ? ቁጥር 7ትን በምናነብበት ጊዜ እነዚህ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በገላትያ አማኞችና በእምነታቸው አካባቢ ሲያደርጉ የሚሞክሯቸው ሁለት ነገሮች ተጠቅሰዋል፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር።
7. በቁ8 ላይ ሐዋርያው "ነገር ግን እኛም ብንሆን ወይም የሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ እርሱ ለዘላለም የተረገመ ይሁን።" በማለት ሲናገር "እኛ" በሚለው አነጋገሩ እነማንን ለማካተት ፈልጎ ወይም ከእርሱ ጋራ ሊጨምራቸው ያሰባቸው ሰዎች እነማን ናቸው?
8. ጳውሎስ በቁጥር 8-9 ላይ የክርስቶስን ወንጌል በማጣመም ላይ ከተሰማሩት ሰዎች ባሻገር ራሱንና የሰማይንም መላዕክት በመጨመር እጅግ ከባድ የሆነ የሚያስፈራ ቃል ይናገራል። ሐዋርያው ለዚህ ነገር ይህንን ያህል ክብደት ለመስጠት የፈለገበት ምክንያት ለምንድነው? የተጣመመና ከእውነተኛው ወንጌል የራቀ ነገር ላለማስተላለፍ ምን ያህል ጥንቃቄ ታደርጋለህ? የወንጌሉን እውነት ስናስተላልፍ በምንችለው መንገድ ሁሉ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ከሁላችንም ይጠበቅብናል።

# ጥናት ሁለት ገላትያ 1፡11-24

የጥናት ዓላማ፡- ሰዎች ከጌታ የተቀበሉትን ደህንነት የሚያጣጥሙበትና ያገኙት ደህንነትም ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ ሳይማሩ በዓለም ታዋቂዎች ስለነበሩ ብቻ ሰይጣን በትዕቢት ሊጥላቸው ወደሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ቸኩሎ ማስገባት ለእነርሱም ሆነ ለቤተ ክርስትያን አደጋን ሊያስከትል እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እነርሱ ግን፣ ቀድሞ እኛን ሲያሳድድ የነበረ ሰው፣ ከዚህ በፊት ሊያጠፋው ይፈልግ የነበረውን እምነት አሁን እየሰበከ ነው የሚለውን ወሬ ብቻ ሰምተው ነበር፤ በእኔም ምክንያት እግዚአብሔርን አመሰገኑ።" ገላ 1፡23-24

1. ገላትያ 1፡11-24 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ11-12 ውስጥ ስንመለከት ጳውሎስ እየሰበከ ያለውን ወንጌል አስመልክቶ የሚናገራቸው አራት ነገሮችን እናያለን፤ እነዚህ አራት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። እነዚህን ቁጥሮች ስናነብ የወንጌል ምንጩ ሰው እንዳልሆነ በተናገረበት ጊዜ እርሱም ራሱ ቢሆን እንኳን የወንጌል ምንጭ እንዳልሆነ ያረጋገጠበት አነጋገር የትኛው ነው ትላለህ?
2. በገላ 1፡11-12 ላይ ጳውሎስ ስለ ወንጌል ምንጭ የሰነዘራቸው ሃሳቦች፣ በ2ኛ ጲጥ 1፡20-21 ላይ ሐዋርያው ጲጥሮስ የሚናገረው ሃሳብ ጋራ ተመሳሳይ ሃሳብን ያስተላልፋሉ ማለት የምንችለው እንዴት ነው?
3. ቁ13-24 ትን ስናነብ ጳውሎስ በሕይወቱ ከእግዚአብሄር ጋራ ያሳለፈባቸውን ሁኔታዎች የሚናገርባቸው ናቸው። በእነዚህን ቁጥሮች ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ የሕይወቱን ሂደት በሶስት የተለያዩ ክፍለ ጊዜያት ከፋፍሎ ሊያሳየን የሞከረበትን ሁኔታ በተረዳኸው መጠን ለማስረዳት ሞክር።
4. ቁ13-14 ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን ከመገናኘቱ በፊት ምን ዓይነት ሰው እንደነበረ ቢያንስ አምስት ነገሮችን ለመዘርዘር ሞክር። እነዚህን ቁጥሮች ማለትም ቁ13ትንና 14ትን ስንመለከት ጳውሎስ በሮሜ 10፡1-3 ውስጥ የአገሩ ሰዎች ስለሆኑት ስለ አይሁዳዊያን የተናገረው ነገር በራሱ ሕይወትም ላይ ሳይቀር የተፈጸመ ነገር እንደ ነበረ ማየት የምንችለው እንዴት ነው። በሰዎች ወግና ሥርዓት ተተብትቦ እግዚአብሄርን ማገልገል ሊመስለን እንደሚችል ከጳውሎስ ሕይወት ምን ያህል ታይቶሃል?
5. ቁ13 ላይ "የእግዚአብሔርንም ቤተ ክርስቲያን እንዴት በእጅጉ እንዳሳደድሁ፣ ለማጥፋትም እንዴት እንደጣርሁ ሰምታችኋል" በማለት ጳውሎስ ስለራሱ የተናገረውን ነገር ስናይና፤ በማቴ 16፡18 ላይ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም" በማለት ስለ ቤተክርስትያኑ የተናገረውን ንግግር ስንመለከት የሚያረጋግጥልን አንድ ወሳኝ እውነት ምንድነው ትላለህ?
6. ቁ15-17ት ላይ ያለውን ሃሳብ ስናነብ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሄር በእርሱ ሕይወት ውስጥ እንደሰራ ወይም እንዳደረገ በእርግጠኛነት የሚናገራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? ይህ ሰው እግዚአብሄር ለሥራው እንደጠራው ግልጽ ሆኖ በታየው ጊዜ ያደረጋቸውና ያላደረጋቸውን ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
7. ቁ18-24 በአንድነት ይነበብ። የጳውሎስ ወደ ክርስቶስ መምጣት በትልቁ ዜና ሊለፈፍና በጊዜው የነበሩት አማኞች ሁሉ ሊያውቁት የሚችሉት ሁኔታ ሲሆን በጌታ ውስጥ ከሶስት ዓመታት ያላነሰ የኖረ እንኳን ቢሆን በአብዛኛዎቹ ሰዎች ገና የታወቀ እንዳልነበረ እናነባለን። የጳውሎስ ዓይነት ትልቅ ቦታ የነበረው ሰው በዘመናችን ጌታን ቢቀበል በጳውሎስ ሕይወት ከሆነው ምን የተለየ ነገር የምናይ ይመስልሃል? ከዚህ ሁኔታስ ምን መማር እንችላለን ትላለህ?

# ጥናት ሶስት ገላትያ 2፡1-10

የጥናት ዓላማ፡- በጳውሎስ ትምህርት ላይ አንዳችም ነገር ሳይጨምሩ ድሆችን እንዳይረሳ እንዳሳሰቡት ሁሉ፤ እኛም በያዝነው እውነት ላይ ሰዎች የሚጨምሩልን ነገር እንደማይኖር ብንረዳም እንኳን፤ የሌሎችን አመለካከት ለመስማትና እግዚአብሄር በእነርሱ በኩል የሚመክረን ነገር ካለ ለመስማት የተከፈተ አዕምሮ ሊኖረን እንደሚገባ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ካገኘሁትም መገለጥ የተነሣ ወደዚያ ሄድሁ፤ በአሕዛብ መካከል የምሰብከውን ወንጌል ለእነርሱም ገለጥሁላቸው። ይሁን እንጂ፣ ምናልባት በከንቱ እየሮጥሁ ወይም ሮጬ እንዳይሆን በመሥጋት፣ ዋነኞች ለሚመስሉት ብቻ በግል ይህን አስታወቅኋቸው።" ገላ 2፡2

1. ገላትያ 2፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ ጳውሎስ ጌታን ከተገናኘ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ እንደነበረ በገላ 1፡18 ላይ እናነባለን። ገላ 2፡ 1 ላይ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገውን ሁለተኛ ጉዞውን ከመጀመሪያው ጉዞው የሚለየው ምን ነገር ትመለከታለህ? ቁ2ትንም ጨምረን ስንመለከት ሁለቱ ጉዞዎች ሌላ የሚለያቸው ሌላ ምክንያት ይጨምርልናል፤ በቁ2 መሰረት ሁለተኛ ጉዞውን ከመጀመሪያው የሚለየው ነገር ምንድነው?
2. ቁ2ን ደግመን ስንመለከት የሄደበትን ምክንያት "ካገኘሁትም መገለጥ የተነሣ ወደዚያ ሄድሁ" በማለት የተገለጠለት ነገር ምን እንደነበረ ግልጽ አድርጎ ባይነግረንም እንኳን፤ እዚያ ከደረሰ በኋላ በመጀመሪያ ያደረገው ነገር ምን እንደነበረ ነግሮናል፤ ይህ ያደረገው ነገር ምን ነበረ?
3. ቁ3 ላይ "ከእኔ ጋር የነበረው ቲቶ እንኳ የግሪክ ሰው ቢሆንም፣ እንዲገረዝ አልተገደደም ነበር።" በማለት መናገሩ ከሐዋርያቱ ጋራ ባደረገው ዝግ ስብሰባ ላይ ስለተካሄደው ውይይት ሊጠቁመን የሚችለው ነገር እንደሚኖር ታስባለህ ወይ? ከሆነስ ያ የሚጠቁመን ሃሳብ ምንድነው ትላለህ? "ሐሰተኞች ወንድሞች" በመባል የሚጠሩት ሰዎች ሃሳባቸውን ለመፈጸም የሚጠቀሙበት ዘዴና እንዲሁም ግባቸው ምን እንደሆነ ከቁ4 በመነሳት አስረዳ።
4. ሐዋርያው ጳውሎስ ዋነኛ ተልኮው አድርጎ የተቀበለው ነገር የክርስቶስን ወንጌል ላላመኑት መናገር እነደሆነ ይታወቃል፤ ሆኖም ቁ5ትን ስንመለከት ወንጌልን ከመስበክ ጋራ አብሮ መሄድ ያለበት ነገር እንዳለና ያንንም ለማድረግ እንደሚጥር እናያለን፤ ይህ ለሰዎች ወንጌልን ከመስበክ ጋራ አብሮ መሄድ አለበት ማለት የሚቻለው ነገር ምንድነው? ከዚሁ ከቁ5 በመነሳት ጳውሎስ ይህንን ተጨማሪ ሃላፊነት ስለተወጣበት ሁኔታ ምን መረዳት ትችላለህ?
5. ቁ6 ላይ "ዋነኛ መስለው ስለሚታዩት ሰዎች ማንነት እኔን አይገደኝም" የሚለው የጳውሎስ አነጋገር የንቀት አነጋገር ሊመስል ይችላል፤ ይህ አነጋገሩ ከንቀት ጋራ ያልተገናኘ መሆኑን ማወቅ የሚቻልበት ምን መንገድ ይኖራል ትላለህ? ታዲያ ይህንን ዓይነት አነጋገር መጠቀም ያስፈለገው መሰረታዊው ነገር ምንድነው ማለት እንችላለን?
6. ሐዋርያው ጳውሎስም ሆነ ሐዋርያው ጴጥሮስ ሁለቱም ወንጌልን ለመስበክ የተጠሩ እንደነበሩ የታወቀ ሲሆን፤ በተለይ ቁ7ትን ስናነብ መልዕክታቸው አንድ ዓይነት ቢሆንም እንኳን ሁለቱን የሚለያቸው አንድ ነገር እንደነበረ ያሳየናል፤ ይህ አንድ ነገር ምን ነበረ? በቁ6 ላይ "እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አያደላም" በማለት ጳውሎስ የተናገረው አነጋገር ቁ8 ላይ ስንመጣ ተፈጻሚ ሆኖ የምናይበት መንገድ እንዴት እንደሆነ አስረዳ።
7. ቁ9-10 ስናነብ ሐዋርያቱ ጳውሎስና ለበርናባስ ወደ አህዛብ እንዲሄዱ የትብብር ቀኝ እጃቸውን ለመስጠት ፈቃደኞች እንዲሆኑ ያደረጋቸው ነገር ምን ነበረ? እኛስ እግዚአብሄር ለሰዎች የሰጣቸውን ጸጋ ለማየት ምን ያህል ጊዜ እንወስዳለን?
8. መለስ ብለን ቁ2ትን ስናይ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚሰብከው ወንጌል ከሐዋርያቱ መልዕክት ጋራ የሚጣጣም መሆኑን ለማረጋገጥ 363 ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዞ መሄዱ ሊያስተምረን የሚችለው አንድ ትልቅ እውነት ምንድነው? በሙሉ ልብህ የተቀበልከውን እውነት ይዘህ፤ እግዚአብሄር ለሌሎች ወገኖች ያስተማራቸውን እውነት ለመስማት ምን ያህል አዕምሮህን ክፍት ታደርጋለህ? ሁላችን እውነት ብለን የምንይዘው ነገር ቢኖረንም እንኳን፤ የሌሎችን አመለካከት ለመስማት የተከፈተ አዕምሮ ሊኖረን ያስፈልጋል።

# ጥናት አራት ገላትያ 2፡11-21

የጥናት ዓላማ፡- ጳውሎስ ሊያስከትልበት የሚችለውን ችግር እያወቀ እውነቱን መጋፈጥ እንደመረጠ ሁሉ፤ እኛም ሊመጣብን የሚችለውን ነገር ፈርተን ሰዎች የወንጌልን እውነት ሲያጣምሙ ዝም ብለን ማለፍ ትክክለኛ አካሄድ እንዳልሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ኬፕሮስ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ፣ በግልጥ ስቶ ስለ ነበር ፊት ለፊት ተቃወምሁት።" ገላ 2፡11

1. ገላትያ 2፡11-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ11 ላይ "ኬፕሮስ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ" ከሚለው አንጋገር በዚያ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ከመገኘቱ አስቀድሞ ሌላ ቦታ እንደነበረ ነው የሚጠቁመን፤ ጲጥሮስ ወደ አንጾኪያ ቤተ ክርስትያን ከመምጣቱ በፊት የት እንደነበረ ተናገር።
2. ቁ11-13 ትን ስናነብ ጲጥሮስ በወንጌል ላይ ያሳየውን ወዲያ ወዲህ መዋዥቅ ወይም ደግሞ ግብዝነቱን ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያሳየን ክፍል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ጲጥሮስ ያሳየውን ግብዝነት የተሞላውን ድርጊት በማያዳግምና ሌሎቹም እያዩና እየሰሙ ጠንከር ባለ መልኩ መገሰጽ ያስፈለገው ለምንድነው?
3. ቁ13 "በርናባስም እንኳ በእነርሱ ግብዝነት እስኪወሰድ ድረስ" የሚለው የጳውሎስ አነጋገር ስለ በርናባስን በዚያ አካባቢ ስለነበረው ሁኔታ ሊጠቁመን የሚችለው አንድ እውነት አለ፤ ይህ እውነት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
4. ቁ14 "ተግባራቸው እንደ ወንጌል እውነት አለመሆኑን በተረዳሁ ጊዜ፣ በሁሉም ፊት ኬፕሮስን እንዲህ አልሁት" ከዚህ አባባሉ እንደምንረዳው የግብዝነትን ተግባር የፈጸመው ጲጥሮስ ብቻውን እንዳልነበረ ማየት እንችላለን። ለምንድነው ታዲያ ጳውሎስ ግሳጼውን በጲጥሮስ ላይ ብቻ ያነጣጠረው? ይህ ክፍል ማንም ሰው ቢሆን የሚያስተምረው ትምህርትና አኗኗሩ የተጣጣሙ ሊሆኑ እንደሚገባ የሚያስተምረን እንዴት እንደሆነ አስረዳ። አንተስ የምትናገረውና የምታስተምረው ነገር ከኑሮህ ጋራ ይጣጣማል ወይ?
5. ቁ14-16 ላይ ጳውሎስ የጲጥሮስን ድርጊት ከወንጌል እውነት ጋራ የማይጣጣም እንደሆን ለማስረዳት በተናገረው ንግግር ውስጥ፤ በተለያየ መንገድ ጽድቅን አስመልክቶ አንድ እውነት አጉልቶ ለመናገር ሲሞክር እንመለከታለን፤ ይህ ሐዋርያው ሊያስተላልፍ የፈለገው  እውነት ምንድነው ትላለህ? "እኛም ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል" በማለት በቁ16 ላይ በተናገረው አነጋገር ላይ "እኛ" የሚለው አነጋገር በእነማን ላይ ያተኮረ ነው?
6. በቁ19 እና በቁ 20 ላይ ጳውሎስ ስለ ራሱ ሲናገር ስለ ሕግ እንደሞተና እንዲሁም ደግሞ ከክርስቶስ ጋራ እንደተሰቀለ ይነግረናል። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ ለመሞቱ ወይም ለመሰቀሉ በምክንያትነት የሚያቀርበው ሃሳብ ምንድነው? ቁ20ን ስናነብ ጳውሎስ በአንድ በኩል እኔ አልኖርም እያለ ሲናገር፤ በሌላ በኩል ደግሞ አሁን እየኖረ እንዳለም በሚናገረው ሃሳብ መሃል የምታየው ቅራኔ አለ ወይስ ሊያስተላልፍ የፈለገው እውነት ምንድነው ብለህ ታስባለህ?
7. ወደ ኋላ መለስ ብለን ቁ11 ላይ ስንመለከት ጳውሎስ "ኬፕሮስ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ፣ በግልጥ ስቶ ስለ ነበር ፊት ለፊት ተቃወምሁት።" በማለት ሲናገር እናያለን። ጳውሎስ ከጲጥሮስ ጋራ መጋጨት እንዳይኖርበት ለራሱ ማሳመኛ ምክንያት ፈጥሮ ማለፍ ይችል ነበረ ብለህ ታምናለህ ወይ? ምን ምክንያት ሊኖረው እንደሚችል ተናገር። አንተስ ሰዎች የወንጌልን እውነት ሲጣመም እያየህ ከጓደኛ ላለመጋጨት ወይም ሌላ ምክንያት በመስጠት ዝም ብለህ ማለፍ የመረጥክበት ጊዜ ይኖራል ወይ? ሊመጣብን የሚችለውን ነገር ፈርተን ሰዎች የወንጌልን እውነት ሲያጣምሙ ዝም ብሎ ማለፍ ትክክለኛ አካሄድ እንዳልሆነ ሊገባን ያስፈልጋል።

# ጥናት አምስት ገላትያ 3፡1-14

የጥናት ዓላማ፡- ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ስለዋጀን፤ ለአባታችን ለአብርሃም የተሰጠው የእግዚአብሄር ጽድቅ እኛም እንደ አብርሃም በእምነት ያገኘነው በረከት ስለሆነ ደህንነታችንንም ከግብ ለማድረስ ከእምነት ሌላ ተጨማሪ ነገር ማስገባት እንደማይኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በዕንጨት ላይ የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው" ተብሎ ስለ ተጻፈ፣ ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን ዋጅቶናል፤ ለአብርሃም የተሰጠው በረከት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ለአሕዛብ እንዲደርስ ዋጅቶናል፤ ይኸውም በእምነት የመንፈስን ተስፋ እንድንቀበል ነው።" ገላ 3፡13-14

1. ገላትያ 3፡1-14 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-5ን ብቻ በማንበብ የገላትያ ሰዎች በሐዋርያው ጳውሎስ የተጠየቋቸው ስንት ጥያቄዎች ታያለህ? ሰው ገና ምንም ያህል በምንባቡ ውስጥ የሰፈረውን ሃሳብ ሳያነብ ጳውሎስ በቁጥር አንድ ላይ የተጠቀመበትን በጣም ጠንካራ ቃላት በማየት በዚያን ወቅት ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ተሰማው ስሜት ምን መናገር ይችላል?
2. በቁ1 አነጋገር እነዚህ የገላትያ አማኞች ከነበሩበት ትክክለኛ አቋም ወደማይረባ የሕግ ጭነት በላያቸው ላይ ለመጫን የሐሰተኛ አስተማሪዎቹ የተጠቀሙበትን መንገድ ለመጥቀስ የተጠቀመበት ቃል ምን የሚል ነው? ቁ2 ላይ "መንፈስን የተቀበላችሁት ሕግን በመጠበቅ ነው ወይስ የተሰበከላችሁን በማመን?" ሲል ጳውሎስ በነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ እንደተከናወነ በእርግጠኛነት የቀበለው አንድ ነገር ምንድነው?
3. በቁ1-5 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ ስንመለከት ጸሐፊው የገላትያ ሰዎች የክርስትና ሕይወታቸውን የጀመሩበትና ሊጨርሱ የሚሞክሩበትን መንገድ ይናገራል። አጀማመራቸውንና ለመጨረስ የሚሞክሩባቸውን መንገዶች በማነጻጸር ተናገር።
4. እንደ ቁ6 እና ቁ7 አነጋገር ከዘመናት ጀምሮ የነበሩትን ክርስትያኖች ማለትም አሁን በዚህ ዘመን የምንገኘውንም አማኞች ጨምሮ ከአብርሃም ጋራ አንድ የሚያደርገን ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
5. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 8፡39 የአብርሃም ልጆች አድርገው ራሳቸውን ለሚመለከቱት አይሁዳውያን "እነርሱም፣ አባታችንስ አብርሃም ነው ብለው መለሱለት። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ የአብርሃም ልጆችስ ብትሆኑ አብርሃም የሠራውን ትሠሩ ነበር።" በማለት የሰጣቸው መልስ በምን መንገድ በገላ 3፡6-9 ላይ ከምናነበው ሃሳብ ጋራ አንድ ዓይነት ሃሳብ እንዳለው ተናገር።
6. የዛሬውን የጥናት ክፍል ስንመረምር ዛሬ ወንጌል በመባል የምናውቀው ሃሳብ በብሉይ ኪዳንም እንደ ዛሬው ግልጽ በሆነ መንገድ አይሁን እንጂ ያኔም እንደነበረ እንረዳለን። በመጀመሪያ ከሁሉ አስቀድሞ ወንጌልን የሰማው ሰው ማን እንደሆነና ወንጌል አብሳሪው ማን እንደነበረ ተናገር። ቁ8 "አሕዛብ ሁሉ በአንተ ይባረካሉ በማለት ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ አስታወቀው" ይህ ክፍል በረከትን ከምን ጋራ ነው አንድ ሲያደርግ የምናየው?
7. ቁ10-12ትን ስናነብ ማንኛውም ሰው ቢሆን ሕግን በመጠበቅ ወደ እግዚአብሄር መቅረብ ወይም ደግሞ መጽደቅ የማይችልበት ምክንያት ለምን እንደሆነ ነው ክፍሉ የሚነግረን?
8. ቁ13-14 ላይ በተለይም ቁ14 "ለአብርሃም የተሰጠው በረከት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ለአሕዛብ እንዲደርስ" በማለት የተነገረው የእግዚአብሄር የቀደመው እቅዱ ተፈጻሚነት አግኝቷል ወይም ደግሞ ተግባራዊ ሆኗል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ለማለት እንደቻልክ አስረዳ። የጽድቅ ኑሮ የጀመርክበት የእምነት ጉዞ ዛሬም በዚያው መንገድ ላይ ነህ ወይስ እንደ ገላትያ ሰዎች ሥራ ቀላቅለህበታል? የክርስትናን ጉዞ በጀመርንበት በእምነት መጓዝ እንጂ ሌላ ተጨማሪ ነገር በእምነት ላይ መጨመር እንደ ገላትያ ሰዎች "የማታስተውሉ" ወይም ደግሞ "ሞኞች" የተሰኘውን ስም ያሰጠናል።

# ጥናት ስድስት ገላትያ 3፡15-29

የጥናት ዓላማ፡- በዓለም ዙሪያ ሁሉ አገራችንንም ጨምሮ ሰዎችን አንዱን ከሌላው ለመለያየትና ለመከፋፈል ዋነኛ ምክንያቶች ሆነው የሚገኙት እንደ ጎሳ፣ ነገድ፣ ዘር፣ ጾታና የመሳሰሉትን ነገሮች በራሳችንም ህይወት ሆነ ሌሎችንም ለልዩነት ማነሳሳት ክርስቶስ ያፈረሰውን የጥል ግድግዳ መልሶ የመገንባት ያህል እንደሚይተናነስ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችሁታልና። በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ ሰው፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ።" ገላ 3፡26-28

1. ገላትያ 3፡15-29 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ15 ላይ "…በዚህም ጉዳይ ቢሆን እንደዚሁ ነው።" በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር፤ ይህ ጉዳይ የሚለው ነገር ከምንባቡ መሃል ከየትኛው ሃሳብ ጋራ እንዳያያዘው ነው የምትረዳው?
2. ሐዋርያው ጳውሎስ በቁ16 ላይ "መጽሐፍ፣ ለብዙ ሰዎች እንደሚነገር፣ ለዘሮቹ አይልም፤ ነገር ግን ለአንድ ሰው እንደሚነገር፣ ለዘርህ ይላል" በማለት የቃላት ምርጫ ብቻ መስሎ የማይታየውን አነጋገር ትልቅ ሥፍራ ሰጥቶት እንመለከታለን። እነዚህ "ለዘርህ" እና "ለዘሮችህ" የሚሉት ሁለት ቃላት ይህንን ያህል ትኩረት ሊሰጣቸው ያስፈለገበት ምክንያት ለምንድነው? ይህ በዚህ ሥፍራ ያየነው ሁኔታ ለግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ምን ሊያስተምረን ይችላል?
3. በቁ15-18 ውስጥ የሰፈረውን ሃሳብ ስንመለከት ሕግና ጸጋ እንደሚቀዳደሙ መረዳት እንችላለን፤ ከህግና ከጸጋ የትኛው ነው ቀዳሚ እንደሆነ የተነገረው? እነዚህኑ ቁጥሮች ስናነብ እግዚአብሄር አምላክ ለባርያው ለአብርሃም ርስትን ለማውረስ የተጠቀመበት መንገድ የጸጋ መንገድ እንደነበረ የሚጠቁመን ጥቅስ የትኛው ነው?
4. አስቀድሞ የመጣው ጸጋ ወይም ደግሞ የተስፋ ቃል ነው ብለን ካልን፤ ታዲያ የሕግ መምጣት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘበት ምክንያት ለምድነው? በቁ21 ላይ ስናነብ ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሄር አምላክ ሕግን የሰጠበት ዓላማ ለዚህ ዓይደለም በማለት የሚናገረው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር።
5. ቁ21 እና ቁ22 ትን ስናይ ሕግ ያንን ያህል ረጅም ዘመናት አስቆጥሮ አንድንም እንኳን ሰው ለማጽደቅ እንዳልቻለ ተስፋው እስከመጣ ድረስ ሁሉም በሐጥያት ሥር እንደነበሩ ይናገራል። ይህ የሆነበት ምክንያት ለምን እንደሆነ ነው ከእነዚህ ቁጥሮች መረዳት የምንችለው?
6. በቁ23-25 ላይ ሕግ እያደረገ የነበረውን ነገርና ተስፋው እስከሚገለጥ ድረስ ከእኛ ጋራ የነበረውን ግንኙነት አስፍሮልናል። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ተስፋ ከመገለጡ በፊት ሕግ ከእኛ ጋራ ስለነበረው ግንኙነት አስመልክቶ ሐዋርያው ያሰፈራቸውን እውነቶች ዘርዝር። ከቁ26 እና ቁ27 ላይ ጨምቀን ማውጣት የምንችላቸው ቢያንስ ሶስት የክርስትና እውነቶች ምን ምንድናቸው?
7. በቁ28 መሰረት በዓለም ሌሎች ሰዎች ለመለያየት የሚጠቀሙባቸው ዘር፣ ጎሳ፣ ቋንቋና ነገድ የመሳሰሉት ሰዎች ክርስትያኖች ጋ ሲመጣ በልዩ መልክ መታየት የሚኖርበት ለምንድነው? አንተስ ዘርን፣ ጎሳን፣ ቋንቋን ወይም ነገድ ከወንድምና ከእህቶችህ እንዲለይህ ያደረከበት ወይም ሌሎች ያንን እንዲያደርጉ ያበረታታህበትን ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ? ክርስቶስ ያፈረሰውን የጥል ግድግዳ መልሰን ለመገንባት የሞከርንበት ጊዜ ካለ ጌታን ይቅርታ በመጠየቅ ወደፊትም ያንን ከመሰለው ተግባር መራቅ ይኖርብናል።

# ጥናት ስድስት ገላትያ 4፡1-20

የጥናት ዓላማ፡- ጳውሎስ ከገላትያ ሰዎች ጋራ የነበረው የሞቀ ግንኙነት እንዳይበላሽ እውነትን ሳይናገር እንዳላለፈ ሁሉ፤ እኛም ከሰዎች ጋራ ያለንን መልካም ግንኙነት እንዳይበላሽብን በመጠንቀቅ የወንጌልን እውነት ከመናገር ወደ ኋላ ማለት እንደማይኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ለመሆኑ ያ ሁሉ ደስታችሁ የት ደረሰ? ቢቻላችሁ ዐይናችሁን ቢሆን እንኳ አውጥታችሁ የምትሰጡኝ እንደ ነበራችሁ እመሰክራለሁ። እውነቱን ስለ ነገርኋችሁ ጠላት ሆንሁባችሁን?” ገላ 1፡15-16

1. ገላትያ 4፡1-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-3ትን ስንመለከት ሕጻን ወራሽና ባሪያ የሚመሳሰሉበት ነገር እንዳለ ይነግረናል። ይህ በሕጻኑ ወራሽና በባሪያው መሃል የተነገረው መመሳሰል ምን እንደሆነ አስረዳ።
2. ቁ4-6 ላይ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በመምጣቱ ምክንያት ከላይ የተመለከትነው ሕጻን ያገኘው ነገር እንዳለ እንመለከታለን። ስለ ኢየሱስ አመጣጥ ሁኔታ ማየት የምትችላቸውን ነገሮች በሙሉ በመዘርዘር ተናገር። በእነዚህ ሶስት ቁጥሮች ውስጥ እንደ ሕጻኑ አድርጎ የሳለን እኛ እንዳገኘነውና እንደተሰጠን አድርጎ የተናገራቸው ምን ነገሮችን ታያለህ?
3. በቁ7 ላይ ሲናገር “ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም” ማለቱ ከአሁን በኋላ እግዚአብሄርን የምታገለግል አይደለህም ማለቱ ነው ወይ? አይደለም የምትል ከሆነ ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ።
4. ቁ8 - 11ድን ስናነብ ሐዋርያው ጳውሎስ የገላትያ አማኞችን የቀደመ ሕይወታቸውንና አሁን አዲስ ያገኙትን ነገር በማነጻጸር የሚናገረው ነገር ምንድነው? አሁን ያሉበትን ሁኔታ ቀድሞ ከነበሩበት ጋራ አነጻጽሮ ካሳያቸው በኋላ መገረም በሞላበት መልኩ የሚያቀርብላቸው ጥያቄዎች ምን እንደሆኑ ተናገር። አንተስ ራስህ በጌታ በመሆንህ የተሰጠህን የልጅነት መብት ምንነት ምን ያህል ከብሮ ይታይህ ይሆን?
5. ጳውሎስ በቁ17-18 ውስጥ “እነዚያ ሰዎች ወደ ራሳቸው ሊወስዷችሁ ይተጋሉ” በማለት ለገላትያ ሰዎች የሚናገረው ስለ የትኞቹ ሰዎች ነው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለእነዚህ የገላትያ አማኞች ተቆርቋሪ በመምሰል ጢጋ ጢጋ በማለት ልባቸውን ሊሰርቁ ስለሚሞክሩት ሰዎች ድብቅ አጀንዳ ጳውሎስ ሊገልጥና ሊያሳያቸው እየሞከረ ያለው እውነት ምንድነው?
6. ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ 4፡15 ላይ “ይልቁንም እውነትን በፍቅር እየተናገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን” በማለት የተናገረውን እውነት በዚህ ክፍል ውስጥ በተግባር እያሳየ ነው ለማለት የሚያስችለን ምን ሃሳብ ታያለህ?
7. በቁ19 ላይ “የምወዳችሁ ልጆቼ ሆይ፤ ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ ስለ እናንተ እንደ ገና ምጥ ይዞኛል” የሚለውን የሐዋርያው ጳውሎስን አነጋገር ስናይ በዚህ ጊዜ ይሰማው ስለነበረው ስሜት ምን መረዳት እንችላለን? ለነዚህ ሰዎች የዚህ ዓይነት ስሜት መሰማቱስ ከምን የመነጨ ይመስልሃል?
8. በቁ 16 ላይ መለስ ብለን ስናይ “እውነቱን ስለ ነገርኋችሁ ጠላት ሆንሁባችሁን?” የሚለው የጳውሎስ አነጋገር ምን ለማለት እንደፈለገ ነው የሚገባህ? ጳውሎስ ከገላትያ ሰዎች ጋራ የነበረውን የሞቀ ግንኙነት ሊያበላሽበት እንደሚችል እያወቀ የወንጌልን እውነት ከመናገር ወደኋላ ላለማለት መወሰኑ ለእኛ ምን ትምህርት ሊሰጠን ይችላል? አንተስ ከሰዎች ጋራ ያለህን ግንኙነት ላለማበላሸት ስትል እውነትን ከመናገር የተቆጠብክበት ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ? ግንኙነትን ላለማበላሸት ሲባል በእውነት ላይ ከመዋሸት መጠበቅ ይገባናል።

# ጥናት ሰባት ገላትያ 4፡21-31

የጥናት ዓላማ፡- የህግ ወኪል ሆኖ የቀረበልን እስማኤል በተስፋ ቃል የተወለደውን ይስሃቅ ላይ እንተነሳበት ሁሉ፤ ዛሬም በራሳቸው ጥረት ጽድቅን ለማግኘት የሚራወጡት ሰዎች ቢሳለቁብንና ከዚያም አልፈው ቢያሳድዱን፤ እኛ የነጻይቷ ልጆች መሆናችንን እንድናስታውስ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ነገር ግን መጽሐፍ ምን ይላል? "ባሪያዪቱን ከልጇ ጋር አስወግዳት፤ የባሪያዪቱ ልጅ ከነጻዪቱ ልጅ ጋር አይወርስምና" ይላል። ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ እኛ የነጻዪቱ እንጂ የባሪያዪቱ ልጆች አይደለንም።" ገላ 4፡30-31

1. ገላትያ 4፡21-31 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ21-23 ውስጥ ጳውሎስ ለሚናገረው ነገር እንደ አድማጮች አድርጎ የሚናገራቸው ሰዎች እነማን ናቸው? በዚህ ሥፍራ ሐዋርያው ስለ ህግ ሊያስተምር የፈለገውን ትምህርት መሰረት አድርጎ የተጠቀመበትን አብርሃምን፤ መጽሐፍ ቅዱሳችን በሌላ ሥፍራዎች ከሕግ ይልቅ ከምን ጋራ ሲያያይዘው ነው የምናውቀው?
2. ቁ22ትን እና ቁ23ትን ስንመለከት ሁለት ሴቶች፣ ሁለት ልጆች እና ሁለት ውልደቶችን እናገኛለን። ጳውሎስ እነዚህን ሁለት ሴቶች ስም ሲሰጣቸው ማንና ማን በማለት ነው የሚጠራቸው? እነዚህ ሴቶች ሁላችን የምናውቃቸውና በሌላ ሥፍራ የሚጠሩበት ስሞቻቸው ማንና ማን እንደሆኑ ተናገር።
3. ቁ23ትን ስታነብ እነዚህ ሁለት ልጆች በእናት መለያየት ብቻ ሳይሆን በአወላለዳቸውም መሃል በጣም ትልቅ የሆነ ልዩነት እንዳለ ክፍሉ ይነግረናል። የአንዱን ልጅ አወላለድ ከሌላኛው ልጅ አወላለድ ልዩ የሚያደርገው ዋነኛ ነገር ምንድነው? ቁ21-24ትን በማንበብ እነዚህ ሁለት ሴቶች ከወለዷቸው ልጆች በላይ በሆነ መንገድ ሁለቱን ኪዳኖች እንደሚወክሉ ተነግሮናል፤ ይህንን ሲል ጸሐፊው ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ አብራራ።
4. በቁ25 እና በቁ26 ላይ ደግሞ እነዚህ ሁለት እናቶች የሚወክሉትን ነገር በሌላ ዓይነት አቀራረብ ሲያስረዳቸው እንመለከታለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሁለቱ ሴቶች የሚወክሏቸው ነገሮች በምን ስም ነው ተጠቅሰው የምናገኛቸው? እነዚህን ቁጥሮች በተለይም ቁ26ትን ስናነብ "እርሷም እናታችን ናት" በማለት ጸሐፊው ራሱን በመጨመር እንደ ነጻዋ ሴትዮ ልጅ በማድረግ ሲናገር፤ ከእርሱ ጋራ የተካተቱት ሰዎች እነማን ናቸው ብለህ ታምናለህ? አንተስ ራስህን በባርነት ካሉት ወይስ ነጻ ከሆኑት መሃል ታያለህ?
5. በቁ27 ሰፍሮ የምናገኘው ጥቅስ ከኢሳይያስ 54፡1 የተወሰደ ሃሳብ ነው። ከላይ ከቁ21 እስከ ቁ26 ካለው ሃሳብ ጋራ በአንድነት ስትመለከተው ይህ ቁጥር 27 ላይ ያለው ጥቅስ ምን ለማለት እንደሆነ ነው የምትረዳው?
6. ከቁ28 እና ቁ29 አነጋገር አንደምንረዳው እነዚህ ሁለት እናቶች የወለዷቸው ሁለቱ ልጆች እርስ በእርሳቸው አብረው ለመኖር እንደማይችሉና አንደኛው ሌላኛውን እንደሚያሳድደው እናነባለን። በዚህ መሰረት አሳዳጁ ማን፤ ተሳዳጁ ደግሞ ማን እንደሆነ በመግለጽ ለወገኖች አስረዳ። በእነዚህ ሁለት ልጆች የተካሄደውን ሁኔታ እንደ ምሳሌ በመከተል፤ ዛሬ ወደ እኛ ዘመን ነገሩን አምጥተህ ስንተረጉመው ምን ማለት ሊሆን ይችላል ትላለህ?
7. ቁ30-31 ትኩረት አድርጎ የሚናገረው የውርስን ጉዳይ እንደሆነና ማን እንደሚወርስ ማን ደግሞ እንደማይወርስ ግልጽ አድርጎ ይናገራል። ውርስ ሁልጊዜ የሚሰጠው ለታላቅ ወይም ለበኩር ልጅ እንደሆነ ሲታወቅ ይህ ክፍል ግን ወራሽ አድርጎ የሚያቀርብልን ማንን ነው?
8. ቁ31 ላይ "ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ እኛ የነጻዪቱ እንጂ የባሪያዪቱ ልጆች አይደለንም።" በማለት ሐዋርያው ያጠቃለለበትን ሃሳብ ስትመለከት ለጊዜው እንደ እስማኤል የሚያፌዙና የሚቀልዱብን ሰዎች ቢበዙም ከዚህ አነጋገሩ ውስጥ ልንቆምበትና ተስፋ ሊሆነን የሚችል ምን ሃሳብ ታያለህ?

# ጥናት ስምንት ገላትያ 5፡1-12

የጥናት ዓላማ፡- ለገላቲያ ሰዎች በእርሾ በመመሰል የተነገረው ሃጥያት ቆይቶ እንደሚሰፋ የተነገረው እውነት፤ ዛሬም በህይወታችን የምንፈቅድላቸው ጥቃቅን መስለው የሚታዩን ሃጥያቶች ነገ እንደ እርሾ ሕይወታችንን የሚቆጣጠሩበት ደረጃ ሊደርሱ ስለሚችሉ ከአሁኑ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሩጫችሁ መልካም ነበር፤ ታዲያ ያሰናከላችሁ፣ ለእውነትስ እንዳትታዘዙ የከለከላችሁ ማን ነው? እንዲህ ያለው ማባበል ከሚጠራችሁ የመጣ አይደለም፤ ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል።" ገላ 5፡7-9

1. ገላትያ 5፡1-12 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1 ላይ "ዳግመኛም በባርነት ቀንበር አትጠመዱ" የሚለውን አነጋገር ስታነብ አንድ የሚጠቁምህ ሃሳብ ምን እንደሆነ ተናገር። አማኞች በክርስቶስ የተገኘ ፍጹም የሆነ ነጻነት እንዳላቸው በዚሁ በቁ1 ላይ ማንበብ እንችላለን። ይህንን በክርስቶስ ኢየሱስ የተገኘውን ነጻነት የመጠበቅ ሃላፊነት እንዳለበት አድርጎ የሚያቀርበው ማንን ነው?
2. በቁ2 እና በቁ3 ላይ ለግርዛት የተሰጠውን ሕግ ለመጠበቅ በአካባቢያቸው እየተመላለሰ ያለውን የግርዛት ትምህርት ተቀብለው የመገረዝ ሃሳብ ላላቸው ሰዎች የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ ምን ነበረ? "የምለውን አስተውሉ፤ ትገረዙ ዘንድ ብትፈልጉ፣ ክርስቶስ ፈጽሞ ለእናንተ እንደማ ይበጃችሁ እኔ ጳውሎስ እነግራችኋለሁ።" በማለት የተናገረው በቁ2 ላይ የሰፈረው ሃሳብ ሐዋርያው ለአንባቢዎቹ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድነው ትላለህ?
3. በሕግ ለመጽደቅ የሚሞክሩ ሰዎች ወይም ደግሞ ከእግዚአብሄር ከሚሰጠው ጽድቅ ይልቅ የራሳቸውን ጽድቅ ሊመሰርቱ ለሚያስቡ ሰዎች ጳውሎስ በቁ4 ላይ የሚናገራቸው ሁለት ዓይነት ማስጠንቀቂያዎችን እንመለከታለን። እነዚህ ሁለቱ ማስጠንቀቂያዎች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር።
4. ገላ 4፡5 "እኛ ግን ተስፋ የምናደርገውን ጽድቅ፣ በመንፈስ አማካይነት በእምነት ሆነን በናፍቆት እንጠባበቃለን።" በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ወደፊት እንደሚገኝና ገና የሚጠበቅ ነገር አድርጎ ነው ጽድቃችንን የሚናገረው፡፡ ይህ ማለት እኛ አማኞች ገና አልጸደቅንም የምንጸድቀው ገና ወደፊት ነው ማለቱ ነው ወይስ በዚህ አነጋገሩ ሊያስተምረንና ሊያስረዳን የፈለገው እውነት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
5. ገላ 3፡2ትን ስናነብ ቲቶ ሳይገረዝ ከጳውሎስ ጋራ አብሮት እንዳገለገለ ሲነግረን፤ የሐዋ ሥራ 16፡3 ደግሞ ጢሞቲዎስን አብሮት እንዲያገለግል ሲወስደው እንደገረዘው እንመለከታለን። ጳውሎስ በራሱ ህይወት ያሳለፋቸው እነዚህ ሁለት ልምምዶች በዚህ ስፍራ በቁ6 ላይ ከተናገረው ሃሳብ ጋራ በምን መንገድ ልናዛምደው እንችላለን ብለህ ታምናለህ?
6. "የሚጠቅመውስ በፍቅር የሚገለጽ እምነት ብቻ ነው።" የሚለው በቁ6 ጳውሎስ የተናገረው ሃሳብ ያዕቆብ 2፥17 እና በ2፡26 ላይ ከተናገረው ሃሳብ ጋራ የሚመሳሰሉት በምን መንገድ ነው?
7. ሐዋርያው ጳውሎስ በቁ11-12 ላይ ስናነብ መስቀልን እንደ ምን አድርጎ ሲናገር ነው የምናየው? ይህ አይነቱ ስለ መስቀል የተነገረው አነጋገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ።
8. ቁ9ኝን መለስ ብለን ስንመለከት ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ማስጠንቀቂያ ምን የሚል ነበረ? በዚያን ዘመን ለነበሩት አማኞች የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ዛሬ ለምንኖር ለእኛ ሕይወት ምን ተግባራዊነት ይኖረዋል ብለህ ታምናለህ? በህይወት ትንሽ ብለህ የምትንቀው ሃጥያት እንዳይኖር የምትችለውን ያህል ጥንቃቄ ልታደርግ ይገባሃል።

# ጥናት ዘጠኝ ገላትያ 5፡13-26

የጥናት ዓላማ፡- አማኝ ከክርስቶስ ጋራ ተሰቅያለሁ በማለት በአንደበቱ ማውራት ብቻ ሳይሆን፤ ከክርስቶስ ጋራ እንደተሰቀለ ማረጋገጫ ሊሆነው የሚችለውን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሕይወቱ ሲያሳይ፤ እንዲሁም ደግሞ ለሥጋው ምኞት ከመገዛት ወጥቶ ለመንፈስ ቅዱስ ሃሳብ እየተገዛ መኖር ሲጀምር እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው። እንደነዚህ ያሉትንም የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር ሰቅለውታል።" ገላ 5፡22-24

1. ገላትያ 5፡13-26 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁጥር 13 ላይ ስናነብ ክርስትያኖች ወይም በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ስለተጠሩበት ጥሪ ምንነት ይነግረናል። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ቁጥር ላይ አማኞች ስለ ተጠሩበት ጥሪ ዓይነት ሶስት እውነቶችን አስፍሮልናል፤ እነዚህ ሶስት እውነቶች ምን ምንድናቸው? በክርስቶስ የሚገኘውን ነጻነቱን የተቀበለና፤ እኔ በቤቴ በግሌ ነው ጌታን የማመልከው፤ በቴሌቪዥን ጥሩ መልዕክቶችን እሰማለሁ፤ ወደ ቤተ ክርስትያን መቀላቀል የግድ አያስፈልገኝም ለሚል አማኝ ይህ ክፍል በቂ መልስ ሊሆነው የሚችለው በምን መንገድ ነው ትላለህ?
2. በገላ 5፡14 ላይ "ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ተጠቃሎአል" በማለት ሲናገር፤ በማቴ 22፡40 ላይ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሕግና ነቢያት በሙሉ በእነዚህ ሁለት ትእዛዛት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው።" በማለት ሲናገር እናየዋለን። በእነዚህ ሁለት ሃሳቦች ያለ የሚመስለውን ቅራኔ የምትመለከትበትን መንገድ አስረዳ።
3. በቁ13-15 ላይ ስናነብ አንዳችን ሌላችንን በፍቅር ማገልገል የነጻነታችን ዓላማና ምልክት እንደሆነ እናነባለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከዚህ ሃሳብ ተቃራኒ ሆኖ መኖር እንደሚቻል የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው? በሁለተኛው አማራጭ በመምረጥ በዚያ መንገድ እሄዳለሁ ካልን ውጤቱ ምን እንደሚሆን ነው ክፍሉ የሚነግረን?
4. ቁ16ትን ስናነብ ሐዋርያው ጳውሎስ በቁ13 ላይ "ነጻነታችሁን ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን መፈጸሚያ አታድርጉት" በማለት የተናገረንን እውነት መፈጸም የምንችልበት ሃይል ምን እንደሆነ በዚህ ቁጥር ላይ ግልጽ ያደርግልናል። ይህንን ለማድረግ የሚያስችለን ሃይል ምንድነው በማለት ነው ቁጥር 16 የሚነግረን?
5. ቁ16-18ትን በማንበብ ሰው አንድን ነገር ለማድረግ ስለፈለገ ብቻ ማድረግ እንደማይችል ወይም የሰው መፈለግ ብቻውን ምንም መፍትሄ እንዳልሆነ እንገነዘባለን። ይህ ክፍል የሰው ልጅ አንድን ነገር ለማድረግ ከልቡ እየፈለገ እያለ ነገር ግን ያንን የፈለገውን ነገር ማድረግ የማይችልበት ምክንያቱ ምንድነው ይለናል? ስለዚህ አማኝ ከሙከራ ሕይወት ወጥቶ ሊከተለው የሚያስፈልገው አንድ መመሪያ ምን መሆን እንደሚኖርበት ተናገር።
6. ቁ16 ጀምሮ ምዕራፉ እስከሚገባደድ ድረስ ያለው ክፍል በሥጋና በመንፈስ ላይ ያተኮረ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በቁ16 ላይ "እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤ የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙም" የሚናገረውን አነጋገር በማየት፤ አማኝ በመንፈስ መኖሩን ወይም ደግሞ የሥጋውን ምኞት እየፈጸመ እንደሆነ ሊያውቅ የምችልበት መንገዱ ምንድነው?
7. ገላ 5፡16-25 ላይ ያለውን ሃሳብ ሁሉ በማንበብ፤ በተለይ በቁ24 ላይ "የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር ሰቅለውታል።" ለሚለው እውነት ሰዎች ሁሉ እውነትም ይህ ሰው ሥጋውን ሰቅሏል ማለት የሚያስችላቸው በክፍሉ መሰረት ምንድነው ብለህ ታምናለህ? በአንተ ሕይወትስ የሚታየው የሥጋ ምኞት ወይስ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ? አማኝ ከክርስቶስ ጋራ እንደተሰቀለ እንደ ማረጋገጫ ሊያሳይ የሚችልበት መንገድ ለሥጋው ምኞት ከመኖር ይልቅ ለመንፈስ ቅዱስ ሃሳብ እየተገዛ መኖር ሲጀምር እንደሆነ ግልስ ነው።

# ጥናት አሥር ገላትያ 6፡1-10

የጥናት ዓላማ፡- ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር አልኝ የሚልና ትዕዛዙን ለመፈጸም የሚፈልግ አማኝ በሙሉ፤ በአጠገቡ ሸክም ከብዶት ሲንገዳገድ የሚያየውን የወንድሙንና የእህቱን ሸክም ለመሸከም ዝግጁና ፈቃደኛ ሊሆን እንደሚገባው ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "አንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም፤ በዚህም ሁኔታ የክርስቶስን ሕግ ትፈጽማላችሁ።" ገላ 6፡2

1. ገላትያ 6፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ ወደ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሳናልፍ ቁ1ድን ብቻ በመመልከት በደልን አስመልክቶ ከዚህ ቁጥር ላይ ልንገነዘባቸው የምንችላቸው ቢያንስ አራት እውነቶች አሉ፤ እነዚህ አራቱ እውነቶች ምን ምን እንደሆኑ አንድ ከቁጥር አንድ ውጭ ሳትወጣ ለመናገር ሞክር።
2. "ወንድሞች ሆይ፤ አንድ ሰው በኀጢአት ውስጥ ገብቶ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ በገርነት ልትመልሱት ይገባል። ነገር ግን አንተም እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ።" ይህ ክፍል የሳተውን ሰው ለመመለስ መንፈሳዊ መሆን እንደሚኖርበት በመናገር፤ ከዚህ ጋራ ደግሞ ድርጊቱን መፈጸም የሚኖርበትንም ሁኔታ አስቀምጧል፤ ይህ ሌላው አስፈላጊ ነገር ምን እንደሆነ ተናገር። "አንተም እንዳትፈተን" የሚለውን ሃሳብ ስንመለከት፤ ይህ ሰው በሃጥያት የተገኘውን ሰው ለመመለስ በሚያደርገው ጥረት ውስጥ እርሱን ሊፈትን የሚችለው ምን ነገር ሊኖር ይችላል ትላለህ?
3. በገላትያ መጽሐፍ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች ከህግ በታች እንዳልሆንን ሐዋርያው ሲያረጋግጥልን ቆይቷል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተለይም በቁ2 ላይ ደግሞ ሌላ መፈጸም ያለብን ሕግ እንዳለ አድርጎ የሚናገረውን ሃሳብ በሌሎቹ ክፍሎች ውስጥ ከሕግ ባርነት ነጻ እንደወጣን ከሚናገራቸው ሃሳብ ጋራ በምን እንደሚለያይና እንዴት ማስታረቅ እንደሚቻል አስረዳ።
4. ቁ3 "አንድ ሰው ምንም ሳይሆን ትልቅ የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላል።" በማለት ይናገራል። ይህ የጳውሎስ አነጋገር ከላይ ሲናገር ከቆየው ሃሳብ ጋራ የሚያያዘው ወይም የሚገናኘው በምን መንገድ ነው ትላለህ?
5. ቁ1-5ትን ስናነብ ሸክምን አስመልክቶ ሁለት ዓይነት የተለያዩ የሸክም ዓይነቶች እንዳሉ እናያለን። እነዚህ ሁለት የሸክም ዓይነቶች ምንና ምንድናቸው?። "እያንዳንዱ የራሱን ሸክም ሊሸከም ይገባዋልና።" የሚለው በቁ5 ላይ የሚገኘውን ሃሳብ ጠለቅ ብለህ ስትመለከት ሸክም ሊኖርባቸው የሚችሉት ሰዎች እነማን ናቸው?
6. በቁ6 ላይ ስናነብ የእግዚአብሄርን ቃል በሚያስተምሩና ቃሉን ደግም በሚማሩት መሃል ሊኖር ስለሚገባው የግንኙነት ዓይነት በሐዋርያው ጳውሎስ በኩል እግዚአብሄር የሚነግረን እውነት ምንድነው? በአንተ አመለካከት የዚህ ዓይነቱን ተግባር ለመለማመድ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች አሉ ብለህ ታምናለህ ወይ? አንዳንዶቹን ለወገኖች ለማካፈል ሞክር።
7. ቁ7-8 አነጋገር መሰረት በመዝራትና በማጨድ መሃል ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት ምን እንደሚመስል ተናገር።
8. በቁ9 እና 10 ላይ ስናነብ ለሰው ልጆች በጎ ነገር እያደረጉ መከሩን እስከማጨድ ድረስ እንዳይደርሱ የሚፈታተኗቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
9. ወደ ኋላ መለስ ብለን ቁ2ትን ስንመለከት ሐዋርያው "አንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም፤ በዚህም ሁኔታ የክርስቶስን ሕግ ትፈጽማላችሁ" በማለት ይናገራል። "የክርስቶስ ሕግ" የሚለውን አብዛኛውን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ከማር 12፡29-31 ካለው ሃሳብ ጋራ ያገናኙታል። ጳውሎስ በቁ2 ላይ ያሰፈረውን ሃሳብ ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? አንተስ ይህንን ሃሳብ በህይወትህ ተግባራዊ ለማድረግ ምን ያህል ልብህ ቆርጧል? ክርስቶስን የሚወድና ትዕዛዙን ለመፈጸም የሚፈልግ ሁሉ፤ የወንድሙንና የእህቱን ሸክም ለመሸከም ዝግጁና ፈቃደኛ የምርጫ ጉዳይ አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል ማለት ነው።

# ጥናት አሥራ አንድ ገላትያ 6፡11-18

የጥናት ዓላማ፡- “አማኝ ሊመካበትና እድሜውን ሁሉ ሊኮራበት የሚችለው በእግዚአብሄር ቃል የተደገፈ አንድ እውነት ቢኖር ዓለም ለእኔ ተሰቅሏል፣ እኔ ደግሞ ለዓለም ተሰቅያለሁ የሚለውን ተቀብሎ መኖር እንደሚኖርበት ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ነገር ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት፣ እኔም ለዓለም ከተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር፣ ሌላው ትምክሕት ከእኔ የራቀ ይሁን።” ገላ 6፡14

1. ገላትያ 6፡11-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ ጳውሎስ በመልዕክቱ ማጠቃለያ ላይ ስንመለከተው ሃሳቡን እያነጣጠረ ያለው በእነማን ላይ ነው ማለት እንችላለን? በቁ12 መሰረት እነዚህ ሰዎች አማኞችን ከጸጋ ወደ ሕግ ለመመለስ የሚከሩባቸውን ሁለት ምክንያቶች አስፍሯል፤ እነዚህ ሁለቱ ምክንያቶች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር።
2. ቁ13ትን ስናነብ “እነርሱ በሥጋችሁ ለመመካት ሲሉ እንድትገረዙ ፈለጉ እንጂ፤ የተገረዙት ራሳቸው እንኳ ሕግን የሚጠብቁ አይደሉም” በማለት ይናገራል። እንዴት ነው አንዱ በተገረዘው ሌላው መመካት የሚችለው?
3. ከላይ በጥያቄ ተራ ቁጥር 2 ላይ  በሥጋቸው ለመመካት እንዲገረዙ የሚፈልጉት ሰዎች ራሳቸው እንኳን ሕግን እንደማይጠብቁ ሐዋርያው ግልጽ አድርጎ ይናገራል። ጳውሎስ በዚህ ሥፍራ እነዚህ ሰዎች ሕግን አይጠብቁም ሲል ምን ለማለት የፈለገ ይመስልሃል?
4. ቁ15 ላይ “መገረዝም ሆነ አለመገረዝ አይጠቅምም” በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ እየተናገረ፤ ለምንድነው ታዲያ በሐዋ ሥራ 16፡3 ላይ ጢሞቲዎስን ሲገርዝ የሚታየው? በዚሁ ቁጥር ላይ ጸሐፊው ወሳኝና ከእግዚአብሄር ጋራ መንገድን ለማስተካከያ ወሳኝ ነገር እንደሆነ አስረግጦ የተናገረለት ነገር ምንድነው? እያንዳንዳችን በውጫዊ ነገር አዕምሯችን ተይዞ ዋነኛውን ነገር ችላ ብለን እንዳንገኝ ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል።
5. ቁ16 ላይ “ይህ ትዕዛዝ” በማለት ጳውሎስ የሚናገርለት ስለየትኛው ትዕዛዝ ነው?
6. ቁ13ትንና ቁ14ትን ስናነብ በጳውሎስና በሃሰተኛ አስተማሪዎቹ መሃል አጉልቶ ለማሳየት የሚሞክረው ትልቅ ልዩነት ምንድነው ትላለህ?
7. ጳውሎስ ትምክህቱን የክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ብቻ የማድረጉ ምክንያት ሌላ ሊመካበት የሚችለው አማራጭ ስለሌለው ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? አይደለም ብለህ የምታምን ከሆነ ግን፣ እርሱ ሊመካበት ይችላል ብለህ የምትላቸው ምን ነገሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ በመዘርዘር ተናገር። በፊሊ 2፡16 መሰረት ጳውሎስ ማንኛውም ዓይነት ትምክህት ካስፈለገ ትክክለኛ ጊዜ እንዳለው በማሳሰብ ጊዜው መቼ ነው ይላል?
8. ቁ14 “ነገር ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት፣ እኔም ለዓለም ከተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር፣ ሌላው ትምክሕት ከእኔ የራቀ ይሁን።” በዚህ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ እኔ ለዓለም ተሰቅያለሁ ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ነው የምትረዳው? አንተስ ዛሬ ለዓለም እንደተሰቀለ ሰው ለመመላለስ እንዳትችል ትግል የሚሆንብህ ነገር ምን ይሆን? ለአማኝ ዓለም ለእርሱና እርሱ ደግሞ ለዓለም እንደተሰቀለ ተቀብሎ ከመኖር የተለየ መጽሐፍ ቅዱሳችን ሌላ አማራጭ እንዳልሰጠን ልንገነዘብ ያስፈልጋል።